# <u>በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።</u>

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን  በጣሊያንና አካባቢው ሀገረ ስብከት የባሪ ደ/ ኃ / ቅ / ጊዮርጊስ በታላቅ ድምቀተ ተከብሮ ዋለ።

ዓመታዊ የሚያዝያ ፳፫/ ፰ /፳፻፲፭ ዓ ም/30/4/2023 የቅዱስ ጊዮርጊስ   በዓለ እረፍቱን ምክንያት በማድረግ
ብፅዕ አቡነ ሕርያቆስ የጣሊያንና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በተገኙበት  በደቡብ ጣሊያን የባሪ ደ/ ኃ / ቅ / ጊዮርጊስ
ቤተክርስቲያን በታላቅ ድምቀተ ተከብሮአል።
ሊቀ ጳጳሱ አርብ ከዋዜማው ቀደም ብለው ከኖሮይ ኦስሎ በ19/ 27 በመነሳት ባሪ አየር ምንገድ ሲደርሱ በደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ኃይል አባ ክብረ ቅዱሳን እና በሰንበት ት/ቤት መዘምራን እና  ምዕመናን በተገኙበት ለብፅዕነታቸውደማቅ አቀባበል ተደርጓል ሊቀ ጳጳሱ አቀባበል ከተደረገላቸው በኋላ ወደማረፊያ ቦታቸው ትውሸኙተዋል፣በማግስቱ ቅዳሜ ሐዋርያዊ ኡደት አድረገዋል ብጹነታቸው  በአካባቢ አንድ አንድ ታሪካዊ ቦታዎችን ሲጎበኙ ዋለው፣እሑድ  ከሌሊቱ አስር ሰዐት ጀምሮ እስከ ጧቱ  ሰዐት የማህሌትና የጸሎተ ኪዳን አገልግሎት ተካሂዶአል፣
 ከጧቱ ሁለት ሰዐት ጀምሮ  በብፅዕነታቸው እየተመራ ስርዓተ ቅዳሴው እስከ ቀኑ አራት ሰዐት ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ከራት ሰዐት ተኩል እስከ አምስት ሰዐት ተኩል በብፁዕ አባታችን የቅዱስ ጊዮርጊስ ታሪክና ተጋድሎ መነሻ በማድረግ ሰፊ የወንጌል አገልግሎት ሰጥተዋል

ብ




የበብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ አቀባበል በባሪ አየር ማረፊያ

ከትምህርቱ በኋላ ተቦታቱ የቅዱስ ጊዮርጊስና የቅድስ አርሴማ   ታቦታት ወጥተው እንደተለመደው ሕዝቡንና አካባቢውን ባርከው በመጨረሻም  ከተለያዩ ከሮም ደብረ ጽዮን ፣ ከደብረ ከነዓን ቅ ስላሴ ፣ከፍሬሲ ቅ ሚካኤል
የመጡ ምዕመናንንና የሰንበት ት ቤ ወጣቶች መዘምራንን በማመስገን ከቀኑ 12:30 ተጠናቋል።




ሊቀ ጳጳሱና ሊቃውንቱ በማሕሌት

በሕይወቴ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ በምኖርበት ዘመን ሁሉ ለአምላኬ እዘምራለሁ።”

መዝሙር ፻፵፮÷፪ በሕይወታችን እንድናመልከው የረዳን የፈቀደልን የአባቶቻችን አምላክ የተመሰገነ ይሁን።